ሸሸኖ ዜና መጽሄት
Sheshino Newsletter
በሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ የውጭና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬት በየወሩ የሚዘጋጅ ዜና መጽሄት
ቁጥር 16 መስከረም 2008 ዓ/ም

# የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ማህበረሰብ በአንደኛው የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቀድ አፈጻጸምና በሁለተኛው እቅድ እንዲሁም በዩኒቨርሲቲያችን 2008 እቅድ ዙሪያ ውይይት አደረገ፡፡

*በመሰረት ታደሰ*

በዩኒቨርሲቲው ከፍተኛ የቦርድ አመራሮችና የዩኒቨርሲቲ ፕሬዝዳንቶች እንዲሁም የቤንች ማጂ ዞን አመራሮች በቅንጅት በሚመሩት የስልጠና መድረክ ከመሽከለም 10 ቀን -2008 ዓም ጀምሮ ለዩኒቨርሲቲያችን መምህራን፣ድጋፍ ሰጭ ሰራተኞችና ተማሪዎች በሶስት ክፍል ለተከታታይ 5 ቀናት በተሰጠው ስልጠና በመላው ተሳታፊ በዘርፈ ብዙ ሃገራዊ ጉዳዮችና ተቋማዊ ጉዳዮች በመማር ማስተማር፣ምርምር፣ማህበረሰብ አገልግሎትና በመልካም አስተዳደር እንደ ሃገር የተመዘገቡ የልማት ውጤቶችን በዝርዝር በመተንተን ሃሳብ የተንሸራሸረ ሲሆን በእያንዳንዱ ነጥብ በተለይ በዩኒቨርሲቲያችን ደረጃ መሻሻል ያሳዩ ጉዳዩችም ተነቅሰው የወጡበት፣በድክመቶቻችን ዙሪያም የተስተዋሉትን ማለትም ከመልካም አስተዳደር ጋር ተያይዞ በደንበኞች እርካታ ረገድ ያለውን ክፍተት በማሳየትና ግብዓት በመስጠት እና የለውጥ እንቅፋቶች ናቸው ያሏቸውንም ለማሳየት የተሞከረበት መድረክ እንደነበር በነበረው የመምህራኖቻችንና ሰራተኞቻችን የስልጠና መድረክ ለመገንዘብ ተችሏል፡፡




**ዶ/ር ዘርይሁን ከበደ የኤፌዴሪ ሰራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ደኤታና የዩኒቨርሲቲያችን አስተዳደር ቦርድ አባል ስልጠና በሰጡበት ወቅት**

በዩኒቨርሲቲያችን ታሪክ የመጀመሪያ በሆነ የሂስ ግለሂስ መድረክም በሁሉም ደረጃ ከከፍተኛ የዩኒቨረሲቲያችን አመራሮች እስከ የታችኛው ፈጻሚ አካል ድረስ ስራን መሰረት ያደረገ የግምገማ መድረክ እንዲፈጠር ከመደረጉም በላይ ውጤቱም በዩኒቨርሲያችን ትልቅ መነቃቃትን የፈጠረ የግለሂስ መድረክ እንደነበር ተገንዝበናል ይህ በራሱ ዩኒቨርሲቲያችን አንድ እርምጃ ወደ ፊት መራመዱን የሚያሳይ እደሆነ ብዙዎች አስተያየት ሰጥተውበታል፡፡



**የስልጠናው ተሳታፊ አስተዳደር ሰራተኞች በከፊል**

የመምህራን አስተዳደር ሰራተኞች ስልጠና በዚህ መልኩ ከተፈጸመ በሗላ ለሁለቱም ግቢዎቻችን ነባር ተማሪችም በተመሳሳይ የውይይጥ ነጥቦች ለአምስት ተከታታይ ቀናት ውይይት በማድረግ ቀላል የማይባሉ ግብዓቶችን በመሰብሰብ ወይይቱ በተሳካ ሁኔታ የተፈጸመ ሲሆን በቀጣይም ወደ ዩኒቨርሲቲያችን ተመድበው ለመጡ ከ4500 በላይ ተማሪዎች ስልጠናው ለአራት ተከታታይ ቀናት ተሰጥቷል፡፡



*ሰልጣኝ ተማሪዎች በክፊል*

# ርዕሰ አንቀጽ

*በመጀመሪያው እድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ያስመዘገብነው ውጤት ለሁለተኛውም ምዕራፍ እቅድ ስኬት መሰረት ነው፡፡*

በመጀመሪያው የዕድገትና ትራንስፎርሜሽን የእቅድ ምዕራፍ እንደ አገር በማይናቅ ደረጃ የልማት ዕቅዶቻችንን ማሳካት ችለናል፡፡ይህ ስኬት ያለህዝባችን ጥረት በዋዛ የተገኘ አይደለም፡፡በስኬቶቻችን ተኩራርተን የምንዘናጋበት ሳይሆን እንደ እቅድ ፈጻሚ አካል አቅማችን በፈቀደ መጠን መሮጥ ይገባናል፡፡

በሂደት የሚገጥሙንን የመልካም አስተዳዳር ችግሮችና እና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶችን በማክሰም የልማታዊ ዴሞክራሲያዊነት የበላይነት አግኝቶ እንዲያብብ የበኩላችንን ጥረት ማድረግ ወሳኝ ይሆናል፡፡ እንደ ሚዛን-ቴፒ ዩቨርሲቲ በቅርቡ ካደረግነው የጋራ ውይይትና የስልጠና መድረኮች ከወሰድናቸው ግብዓቶች በመነሳት ችግባሮቻችንን በየጊዜው በመፈተሽ ፈጣን ምላሽ የመስጠት ልምዳችንን ማጎልበት ወሳኝ በመሆኑ መላው የዩኒቨርሲቲያችንም ማህበረሰብ ምንግዜም ለችግሮ ፈጣን የመስጠት ልምዳችንን ከፍ በማድረግ የለውጥ ጉዟችን ይሳለጥ ዘንድ በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ የመልካም አስተዳደርና የኪራይ ሰብሳቢነት አመለካከቶችን የመጸየፍ ባህላችንን ማሳደግ ተገቢ ይሆናል፡፡

በመማር ማስተማር ዘርፍ በ2007ዓ/ም የተገኘው መልካም የሚባል የሚበረታታ ውጤት ሳይቀዛቀዝ መቀጠል ስለሚኖርበት በፈጠርናቸው አደረጃጀቶች ማለትም የ1ለ5 አደረጃጀታችን በስፋት ተጠናክረው እንዲቀጥሉ በማድረግና አደናቃፊ አመለካከቶችን በልማታዊ አስተሳሰብ እዲዋጥና እንዲቀለበስ በመስራት በሌሎችም የትኩረት መስኮቻችን እንደ ከፍተኛ ትምህርት ተቋም የማህበረሰባችንን ችግሮች የሚፈቱና ዘለቄታዊ ምላሽ ሊሰጡ በሚችሉ የጥናትና ምርምር ስራዎቻችን

ላይ በስፋት በማተኮር ለሁለተኛው በዕድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅድ ስኬት የመጀመሪያውን የዕድገትና ትንስፎርሜሽን ውጤት መሰረት በማድረግ ሃይላችንን አሟጠን በመጠቀም ዛሬም ልንረባረብ ይገባል፡፡በመጨረሻም ከከፍተኛ አመራር እስከ ታችኛው ፈጻሚ አካል ባንድ አላማና ልብ ሆነን ለዩኒቨርሲቲያችን ራዕይና ተላዕኮ ስኬት እንስራ፡

## የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ርዕሰ መስተዳድር የተከበሩ አቶ ደሴ ዳልኬ የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲን የስራ እንቅስቃሴ ጎበኙ፡፡

*በመሰረት ታደሰ*

ረቡዕ ጥቅምት 3 ቀን 2008 ዓ/ም በዩኒቨርሲቲው ዋና ግቢ የተገኙት ርዕሰ መስተዳድሩ በዩኒቨርሲቲው ልዩ ትኩረት ተሰጥቶባቸው በመከናወን ላይ ያሉትን የነባርና አዲስ ህንጻዎች ግንባታ ሂደት ተዘዋውረው ጎብኝተዋል፡፡ በጉብኝታቸው ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ በቅርቡ ለሚቀበላቸው ከ4500 በላይ አዲስ ተማሪዎቹ አገልግሎት የሚውሉ የመማሪያ ክፍሎች የተማሪዎች ማደሪያ ዶርሞችን እና በአዲስ መልክ ጥገና ተደርጎለት አገልግሎት የሚሰጠውን የተማሪዎች መመገቢያ አዳራሽ ተመልክተዋል፡፡



**አቶ ደሴ ዳልኬ ዩኒቨርሲቲያችንን ተዘዋውረው ሲጎበኙ**

ርዕሰ መስተዳድሩ ግቢውን ተዘዋውረው ከመጎብኘታቸው አስቀድሞ የዩኒቨርሲቲውን የመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎቴች በክፌል በሚያሳይ ስዕላዊ መግለጫ አማካኝነት በዩኒቨርሲቲያችን የህዝብ ግንኑኝነት ባለሞያዎች ማብራሪያ ተደርጎላቸዋል፡፡



ዩኒቨርሲቲያችን ስላከናወናቸው የመማር ማስተማር፣ ምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ስራዎች ማብራሪያ ሲደረግላቸው

አቶ ደሴ ዳልኬ በጉብኝታቸው ማጠቃለያ በሰጡት አስተያየት አሁን በዩኒቨርሲቲው እየታየ ያለው ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴ የበለጠ ተጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባው ገልጸው ዩኒቨርሲቲው አሁን የያዘው አጠቃላይ ይዞታ በሚመለከት ለወደፊት ለሚያደርጋቸው የማስፋፊያ ግንባታዎችና የተማሪ ቅበላ አቅሙን በሚያሳድግበት ጊዜ የተመቻቸ ሁኔታ ከመፍጠር አንጻር ተጨማሪ ይዞታ ስለሚያስፈልገው ከወዲሁ ይዞታውን የማስፋቱ ጉዳይ ሊታሰብበት እንደሚገባ አጥብቀው አሳስበዋል፡፡

## የመሠረታዊ ህብረት ሥራ አመራር ሥልጠና ማህበራትን የማቀራረብ ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑ ተስተውሏል

*በተከተል ጳውሎስ*

መንግሥት በርካታ የህብረት ሥራ ማህበራትን በተለያየ ደረጃ በማቋቋም ዜጎች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ባህል እንዲያዳብሩ ለማድረግ በርካታ ተግባራትን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በዚሁ ረገድ በዩኒቨርሲቲያችን ተቋቁሞ ከ40 በላይ አባላትን የያዘ የሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ መምህራንና አስተዳደር ሠራተኞች የገንዘብ ቁጠባና ብድር ማህበር አንዱ የቅርብ ማሳያ ነው፡፡

ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲም የመንግሥት ተልዕኮ ለማሳከት ቀደም ሲል በትምህርት ጥራት፤ በግብርናና ገጠር ልማት፤ በጋዜጠኝነት ሥነ-ምግባር በመሳሰሉ ዘርፎች ሥልጠናዎችን ለተለያዩ አካላት በተለያየ ደረጃ በመስጠት የማህበረሰብ ድጋፍ ተልዕኮውን ለመወጣት ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

ከዚሁ ጋር ተያይዞ የዩኒቨርሲቲያችን ቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ የህብረት ሥራ ትምህርት ክፍል ከማህበረሰብ

ልማት ድጋፍ ተቋም ጋር በመተባበር ከጥቅምት 2 ቀን 2008 ዓ/ም ጀምሮ ለ4 ቀናት የቆየ ሥልጠና ከተለያዩ የመሠረታዊ ህብረት ሥራ ማህበራት ለመጡ ወደ 40 ለሚሆኑ አመራር አከላት ሰጥቷል፡፡






*የማህበራቱ የቡድን ውይይትና የልምድ ልውውጥ ሂደት*

ሥልጠናው የህብረት ሥራ ጽንሰ-ሀሰብ፤ የህብረት ሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ፤ ከተለያዩ ክልሎች የተቀመሩ ምርጥ የህብረት ሥራ ተሞክሮዎች፤ የህብረት ሥራ አስተዳደርና አመራር፤ የንብረት አስተዳደርና አያያዝ፤ የህብረት ሥራ ሂሳብና መዝገብ አያያዝ ወዘተ መሠረታዊ ሀሰቦች ላይ ጠለቅ ያለ ገለጻ የተደረገበት ነበር፡፡ ሠልጣኞቹም በወቅቱ በቡድን ውይይት በማድረግ፤ የማህበራት ተሞክሮና ልምድ በመለዋወጥ እንዲሁም በተለያየ ደረጃ ሪፖርት በማቅረብ በከፍተኛ ትኩረት ሥልጠናውን መከታተላቸው ለመገንዘብ ተችሏል፡፡

በመጨረሻም የህብረት ሥራ ትምህርት ክፍል ኃላፊ መምህር ማቴዎስ ኃይሌ፤ ሥልጠናው በቀጣይ በስፋትና በጥልቀት የሌሎች ማህበራት አመራሮችን በሰፊው በማሳተፍ አሁን ከተገኘው ግብዓት ጋር በአግባቡ በማዋሂድ የሚቀጥል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ሠልጣኞችም በበኩላቸው የሥልጠናው እድል በዩኒቨርሲቲው በመዘጋጀቱ ያላቸውን አድናቆትና ምሥጋና አቅርበው ስልጠናው በቀጣይነት ከሌሎች ማህበራት ጋር የልምድ ልውውጥ በማድረግ አቅማችንን የምንገነባበት እድል ይበልጥ ቢመቻች ብለዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲያችን የውጭና ህዝብ ግንኙነት ዳይሬክቶሬትም የማህበረሰብ ልማት ተቋም ከኮሌጁ የትምህርት ክፍል ጋር በመሆን ያዘጋጀው የመሠረታዊ የህብረት ሥራ አመራር አካላት ሥልጠናው በማህበራት የሥራ አፈጻጸምና በመሠረታዊ ጽንሰ-ሀሰቦች ዙሪያ ግንዛቤ ከማስጨበጡም ባሻገር ልዩልዩ ማህበራትን የማቀራረብ ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑ የተስተዋለበት በመሆኑ በሌሎች ዘርፎችም የማህበረሰብ ልማት ድጋፍ አገልግሎት ተጠናክሮ ይቀጥል እንላለን፡፡

## *ሚዛን-ቴፒ ዩኒቨርሲቲ ያደረገልን ድጋፍና የአቅም ግንባታ ስልጠና ተስፋችን ይበልጥ ብሩህ እንዲሆን አግዞናል ሲሉ በደማቸው ኤች አይ ቪ/ኤድስ ቫይረስ የተገኘባቸው በሚዛንና አማን ከተማ የሚኖሩ ወገኖች ገለጹ፡፡*

ለአንድ አገር ኤኮኖሚያዊ እድገት የሰው ሃብት የሚኖረው ድርሻመተኪያ የለውም፡፡ ይህም በመሆኑ ጤናው የተጠበቀ ምርታማ ዜጋ ለመገንባት የረዥም፣የመካከለኛና የአጭርጊዜ እቅድ አቅዶ መንቀሳቀስም ተገቢም ነው፡፡በመላው ዓለማችን ከጥቂት አጭር ዓመታት በፊት የስርጭት አድማሱን በማስፋት በአጭር  ጊዜ ውስጥ ይህ ነው የማይባል አስከፊ ጥፋት በማድረስ በአገራት ኤኮኖሚያዊና ማህበራዊ እድገት ላይ ጫና በመፍጠርም ላ ይገኛል፡፡ ኤት አይቪ ኤድስ ፡፡ የቫረሱን  ስርጭት ለመቀነስ በመላው አለም አገራት ኤኮኖሚያቸው በፈቀደ  ለበሽታው በሰጡት ግምትና ትኩረት መጠን እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፡፡ኢትዮጵያም የተለያዩ ስትራቴጅዎችን ነድፋ መስራት ከጀመረች አመታት ተቆጥረዋል፡፡ በስትራቴጅው ከተቀመጡት ስልቶች ዋናው ስለ በሽታው ምንነት ለማህበረሰቡ በቂ ትምህርት በመስጠት ግንዛቤ ማስጨበጥ ስራ በሰፊው መስራት ዋናው ጉዳይ ሆኖ ሌሎቹን የመከላከያ ዘዴዎችንም መተግበር ሁለተኛው አማራጭ ሆኖ ቆይቷል፡፡ከመከላከሉ ስራ ጎን ለጎን በደማቸው ቫይረሱ የተገኘባቸው ሰዎች የሚደርስባቸውን ኢኮኖሚያዊ ችግር ለማቃለል በተለያዩ የገቢ ማስገኛ ተግባራትን በማሰማራት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ስልት መቀየስ ወሳኝ በመሆኑ ሚዛን-ቴፒ በማህበረሰብ

አገልግሎት እንቅስቃሴው በሚዛንና አማን ከተማ ከቫይረሱ ጋር ለሚኖሩ ወገኖች የ3 ቀን የአቅም ግንባታ ስልጠና የሰጠ ሲሆን 50 ለሚሆኑ ወገኖችም የተሻሻሉ የበግ ዝርያዎች ገዝቶ ለመርዳትና የገቢ ምንጭ እንዲፈጥሩ ለማስቻል ዝግጅት የተጠናቀቀ ሲሆን በስልጠናው ግለሰቦቹ በዘርፉ ሲሰማሩ ስራውን ውጤታማ በሆነ ሁኔታ እንዲያከናውኑም ስልጠናው እንደሚረዳቸው ታውቋል፡፡ በስልጠናው መክፈቻ ስነ-ስርዓት ላይ የተገኙት አቶ ጸጋዬ ማሞ የመ/ማ/ም/ማ/ል/ድ/ምክትል ፕረዝዳንት ባደረጉት ንግግር ከቫይረሱ ጋር የሚኖሩ ወገኖች እንደማንኛውም የህብረተሰባችን ክፍሎች ሁሉ በተለያዩ የስራ ዘርፎች ተሰማርተው ውጤታማ መሆን እንደሚችሉ ገልጸው ሚዛን-ቴፒ ዩቨርሲቲም በዚህ ዘርፍ ለተሰማሩ የህብረተሰባችን ክፍሎች ድጋፍ ማድረጉን እንደሚቀጥል አስረድተዋል፡፡

ዶ/ር ከለለው አዲሱ የዩኒቨርሲቲያችን ምርምርና ማህበረሰብ ድጋፍ ተቋም ዳይሬክተር በበኩላቸው ስለ ስልጠናው ጠይቀናቸው ዳይሬክቶሬቱ በሌሎች ሆነ በተመሳሳይ ዘርፎች ለማህበረሰባችን የሚሰጡ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎች ተጠናክረው እንደሚሰጡና በተለይም በዚህ አይነት ሁኔታ ለሚገኙ ወገኖች ይህን መሰል ድጋፍ ማድረግ የሚበረታታና ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚገባም አስረድተዋል፡፡